# የሐዋርያት አመክንዮ

ርዕሰ አድባራት ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቤዛ-ኵሉ ሰንበት ት/ቤት
RE'ESE ADBARAT TSREHA ARYAM KIDIST SELASSIE ETHIOPIAN ORTHODOX TEWAHEDO CHURCH BEZA-KULU SUNDAY SCHOOL
ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ MINNEAPOLIS MINNESOTA

፩- አስቀድመን እንደተናገርን በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውም፡፡

፪- የማይጠፋ ብርሃን አለው፡፡ ወደ እርሱ መቅረብ የሚቻለው የለም፡፡

፫- ሁለተኛ አይደለም፣ ሦስተኛም አይደለም፣ አይጨመርበትም፤ ብቻውን ለዘላለሙ የሚኖር አንድ ነው እንጂ፡፡

፬- የማይታወቅ የተሰወረ አይደለምና፡፡ ሁሉን የያዘና ከፍጥረቱም በላይ የሰለጠነ መሆኑን፤ በኦሪትና በነቢያት ፈጽመን አወቅነው እንጂ፡፡

፭- የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡

፮- ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ፣ ከእርሱ ጋር የተካከለ የሚሆን አንድ ልጅ፣ ሠራዊትንና ሊመታትን ሥልጣናትንም ሁሉ የፈጠረ፡፡

፯- በኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ የወደደ፡፡ ያለ ዘርዐ ብእሲ ቅድስት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ነሣ፡፡

፰- ያለ ኃጢአትና በደል እንደ ሰው አደገ፡፡

፱- በአንደበቱ ሐሰት የለበትም፡፡

፲- ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ ሞተ ተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፡፡

፲፩- ወደ ላከው ወደ አብ ወደ ሰማይ ዐረገ፡፡

፲፪- ኃይል ባለው ቀኝ ተቀመጠ፡፡

፲፫- ከአብ የሰረጸ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን ሰደደልን፡፡ ዓለሙንመ ሁሉ አዳነ፡፡ ከአብና ከወልድ ጋር ሕልው የሚሆን፡፡

፲፬- እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልበትም እንደሌለ እንናነገራለን፡፡ ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሯቸዋልና፡፡

፲፭- የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽሕት ቅድስት ናት፡፡

፲፮- እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን፡፡ ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሯቸዋልና፡፡

፲፯- ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስ እንዳለን በሥጋችን እናስተውል፡፡

፲፰- እኛስ የሃይማኖት ለዋጮችን ሥራቸውን እንጸየፋለን፤ መለየታቸውንም ሁሉ፤ ሕግ መለወጣቸውንም፡፡ እነርሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና፡፡

፲፱- ዳግመኛም የሞቱ የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ እንዳለ እናምናለን፡፡

፳- ሁሉ እንደ ሥራው ፍዳውን የሚቀበልበት የፍርድ ቀንም እንዳለ እናምናለን፡፡

፳፩- ዳግመኛም ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ ተነሣ ምንም ሕፀፅ እንደሌለበት እናምናለን፡፡ በእውነት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ፡፡

፳፪- የአብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፡፡

፳፫- እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር ኦሪትንና ነቢያትን የሚፈጽማቸው እንደመጣ እናውቃለን፡፡

፳፬- አሕዛብ ሁሉ የእርሱን መምጣት ተስፋ የሚያደርጉት ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ከእሴይም ሥር የተገኘ ሥልጣኑ በትከሻው ላይ የሆነ ነው፡፡

፳፭- ክብርና ምስጋና ገናናነት፤ ቡራኬና ውዳሴ መመስገን፤ ለእርሱ ይገባዋል፡፡ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን!

### ፩) አስቀድመን እንደተናገርን በዘመኑ ሁሉ ይኖራል እንጂ፤ ጥንት ወይም ፍጻሜ የለውም፡፡

- ❖ አግዚአብሔር ሙሴን...ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ብሎታል። ዘጸ. ፫፡፲፬
- ❖ አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም። ኢሣ. ፵፡፳፰
- ❖ ተራሮች ሳይወለዱ፥ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ። መዝ. ፺፤፪
- ❖ አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማያትም የእጅህ ሥራዎች ናቸው፡፡ እነርሱ ይጠፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ፤...አንተ ግን ያው አንተ ነህ ዓመቶችህ ከቶ አያልቁም›› (መዝ. ፻፩፡፳፭-፳፯)

### ፪) የማይጠፋ ብርሃን አለው፡፡ ወደ እርሱ መቅረብ የሚቻለው የለም፡፡

- ❖ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ። ዘጸ. ፴፫፡፳
- ❖ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።ዮሐ. ፩፡፲፰
- ❖ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል። ዮሐ. ፬፡፳፬
- ❖ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን። ፩ጢሞ. ፮፡፲፮
- ❖ እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል። ፩ዮሐ. ፬፡፲፪

### ፫) ሁለተኛ አይደለም፣ ሦስተኛም አይደለም፣ አይጨመርበትም፤ ብቻውን ለዘላለሙ የሚኖር አንድ ነው እንጂ፡፡

- ❖ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። ዘዳ. ፮፡፬
- ❖ ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን። ፩ጢሞ. ፩፡፲፯
- ❖ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ። ኤፌ. ፬፡፭-፮

### ፬) የማይታወቅ የተሰወረ አይደለምና፡፡ ሁሉን የያዘና ከፍጥረቱም በላይ የሰለጠነ መሆኑን፤ በኦሪትና በነቢያት ፊጽመን አወቅነው እንጂ፡፡

- ❖ ቃሌን ስሙ፤ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፥ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ዘኍ. ፲፪፡፮
- ❖ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን። ዕብ. ፩፡፩-፪
- ❖ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። ማቴ. ፭፡፲፯
- ❖ ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። ዘኍ. ፳፫፡፲፱

### ፭) የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አንድ ነው፡፡

- ❖ እኔ አምላክ ነኝና ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ እንደ እኔ ያለ ማንም የለም። ኢሣ. ፵፮፡፱
- ❖ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። ዘዳ. ፮፡፬
- ❖ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም ሌላ ማንም የለም፤ ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤ በፀሐይ መውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስታጠቅሁህ፥ አንተ ግን አላወቅኸኝም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከእኔም ሌላ ማንም የለም። ኢሣ. ፵፭፡፭-፮
- ❖ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። ኢሣ. ፵፬፡፮

**፭) ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ፣ ከእርሱ ጋር የተካከለ የሚሆን አንድ ልጅ፣ ሠራዊትንና ሲመታትን ሥልጣናትንም ሁሉ የፈጠረ።**

- ❖ እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው። የሚታዩትና የማይታዩትም፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው። ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል። እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል። ቆላ.፩፡፲፭-፲፯
- ❖ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን። ፩ቆሮ.፰፡፮
- ❖ ያዳነን በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ አሳብና ጸጋ መጠን እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ <u>ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን።</u> ፪ጢሞ. ፩፡፱
- ❖ አባት ሆይ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ። ዮሐ.፲፯፥፭

**፮) በኋለኛው ዘመን ሰው ይሆን ዘንድ የወደደ። ያለ ዘርዐ ብእሲ ቅድስት ከምትሆን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ነሣ።**

- ❖ ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ። ገላ. ፬፡፬
- ❖ ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል። ...ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። ማቴ. ፪፡፩-፪

**፯) ያለ ኃጢአትና በደል እንደ ሰው አደገ።**

- ❖ ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር። ሉቃ. ፪፡፶፪
- ❖ እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም። ፩ዮሐ.፫፡፭
- ❖ እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ፩ጴጥ. ፪፡፳፪
- ❖ እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። ፪ቆሮ. ፭፡፳፩

**፰) በአንደበቱም ሐሰት የለበትም።**

- ❖ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም። ማር. ፲፫፡፴፩
- ❖ እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ራእ. ፳፪፡፲፫
- ❖ ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን? ዘኍ. ፳፫፡፲፱

**፱) ከዚህ በኋላ በሥጋ ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ።**

- ❖ ማቴ. ፳፯ እና ፳፰ /ጠቅላላ ምዕራፍ ማር. ፲፭ እና ፲፮/ጠቅላላ ምዕራፍ
- ❖ ሉቃ. ፳፫ እና ፳፬/ ጠቅላላ ምዕራፍ ዮሐ. ፲፱፣ ፳ እና ፳፩/ጠቅላላ ምዕራፍ

**፲) ወደ ላከው ወደ አብ ወደ ሰማይ ዐረገ።**

- ❖ ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው። እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም። የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሏቸው። ሐዋ. ፩፡፱-፲፩
- ❖ ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ። ማር. ፲፮፡፲፱
- ❖ ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ። ሉቃ. ፳፬፡፶፩
- ❖ አምላክ በእልልታ፥ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ። መዝ. ፵፮፡፭

## ፲፪) ኃይል ባለው ቀኝ ተቀመጠ።

- ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ። ማር. ፲፮:፲፱
- እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥ ዕብ. ፲:፲፪
- ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል። ሉቃ. ፳፪:፷፱
- እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ፥ ሁሉን በስልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ። ዕብ. ፩:፫
- ...የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና። ዕብ. ፲፪:፩-፪
- እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ። ፩ጴጥ. ፫:፳፪
- የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ሮሜ. ፰:፴፬

## ፲፫) ከአብ የሰረጸ ጰራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስን ሰደደልን። ዓለሙንም ሁሉ አዳነ። ከአብና ከወልድ ጋር ሕልው የሚሆን።

- ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል። ዮሐ. ፲፭:፳፮
- እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ። ፩ዮሐ. ፪:፪
- ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ። ፩ጢሞ. ፩:፲፭
- እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን። ፩ዮሐ. ፬:፲፬
- በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ። እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ። ዮሐ. ፩:፳፱
- እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። ማቴ. ፳፰:፲፱-፳
- ...ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ? ሐዋ. ፭:፫
- ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን? ዕብ. ፱:፲፬
- <u>የእግዚአብሔርን ልጅ</u> የረገጠ ያንንም <u>የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም</u> እንደ ርኵስ ነገር የቆጠረ <u>የጸጋውንም መንፈስ</u> ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? ዕብ. ፲:፳፱

## ፲፬) እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ በጎ እንደሆነ የሚጣልበትም እንደሌለ እንናገራለን። ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሯቸዋልና።

- እግዚአብሔር የምድር አራዊትን እንደ ወገኑ አደረገ፥ እንስሳውንም እንደ ወገኑ፥ የመሬት ተንቀሳቃሾችንም እንደ ወገኑ አደረገ፤ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው። ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት። እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን። ዘፍ. ፩:፳፭-፴፩
- እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፥ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም። ፩ጢሞ. ፬:፬

## ፲፭) የሥጋ ሕይወት የምትሆን ነፍስ ግን ንጽሕት ቅድስት ናት።

- ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው ሥጋ ምንም አይጠቅምም የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።ዮሐ. ፮:፷፫
- የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ...የእንስሳም ነፍስ ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማን ነው? መክ. ፫:፳፩
- አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ። መክ. ፲፪:፯

**፲፮) እኛስ ጋብቻ ንጹሕ እንደሆነ ልደትም ርኩሰት እንደሌለበት እንናገራለን። ሕዝቡ ይበዙ ዘንድ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሯቸዋልና።**

- እግዚአብሔርም አለ። ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ ...እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። ዘፍ. ፩፡፳፮-፳፰
- እግዚአብሔር የሕይወትን መንፈስ አንድ አድርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድር ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፥ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ...ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ። ሚል. ፪፡፲፭-፲፮
- መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ዕብ. ፲፫፡፬

**፲፯) ከሥጋ ጋር የማትሞትና የማትበሰብስ ነፍስ እንዳለን በሥጋችን እናስተውል።**

- ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ። ማቴ. ፲፡ ፳፰
- የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማን ነው? መክ. ፫፡፳፩
- አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ። መክ. ፲፪፡፯

**፲፰) እኛስ የሃይማኖት ለዋጮችን ሥራቸውን እንጸየፋለን፤ መለየታቸውንም ሁሉ፤ ሕግ መለወጣቸውንም። እነርሱ በእኛ ዘንድ የረከሱ ናቸውና።**

- ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና። ፪ዮሐ. ፱-፲፩
- ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ። ወደ ቤቶች ሾልከው እየገቡ፥ ኃጢአታቸው የተከመረባቸውን በልዩ ልዩ ምኞትንም የሚወሰዱትን ሁልጊዜም እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉትን ሞኞችን ሴቶች የሚማርኩ፥ ከእነዚህ ዘንድ ናቸውና። ኢያኔስና ኢያንበሬስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፥ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ አእምሮአቸው የጠፋባቸው ስለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው፥ እውነትን ይቃወማሉ። ዳሩ ግን የእነዚያ ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ፥ ሞኝነታቸው ለሁሉ ይገለጣልና ከፊት ይልቅ አይቀናላቸውም። ፪ጢሞ. ፫፡፩-፱

**፲፱) ዳግመኛም የሙቱ የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ እንዳለ እናምናለን።**

- ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ። ራእ. ፳፡፲፪-፲፫
- ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል። ማቴ. ፲፩፡፳፭
- ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ፥ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች? ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ። በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም። ማቴ. ፳፪፡፳፰-፴

**፳) ሁሉ እንደ ሥራው ፍዳውን የሚቀበልበት የፍርድ ቀንም እንዳለ እናምናለን።**

- እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ራእ. ፳፪፡፲፪-፲፫
- እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል። ማቴ ፲፪፡፴፮

**፳፩) ዳግመኛም ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ የተነሣ ምንም ሕፀፅ እንደሌለበት እናምናለን። በእውነት ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ።**

- ❖ ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ፥ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር፥ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር። ኢሣ.፶፫፥፱
- ❖ የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም። ዕብ. ፪፥፲፮
- ❖ ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ። እነሆ፥ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው። ዮሐ. ፲፱፥፬
- ❖ ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት፤ እነሆም፥ በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም። ሉቃ. ፳፫፥፲፬
- ❖ እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። ዮሐ. ፲፰፥፴፯

**፳፪) የዕብ ሊቀ ካህናት የሚሆን እርሱ የሰውን ባሕርይ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።**

- ❖ ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን። ሮሜ. ፭፥፲
- ❖ ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን። በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። ፪ቆሮ. ፭፥፲፰-፳፩
- ❖ እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ። ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም። ዕብ. ፬፥፲፬-፲፭
- ❖ በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው፥ ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ። ዕብ. ፮፥፳

**፳፫) እንግዲህ እንደ አይሁድ አንገዘር ኦሪትንና ነቢያትን የሚፈጽማቸው እንደመጣ እናውቃለን።**

- ❖ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። ሉቃ. ፳፬፥፵፬
- ❖ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። ገላ. ፭፥፮
- ❖ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና። ገላ. ፮፥፲፭
- ❖ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። ማቴ. ፭፥፲፯

**፳፬) አሕዛብ ሁሉ የእርሱን መምጣት ተስፋ የሚያደርጉት ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ከእሴይም ሥር የተገኘ ሥልጣኑ በትከሻው ላይ የሆነ ነው።**

- ❖ ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ኢሣ. ፱፥፮

**፳፭) ክብርና ምስጋና ገናናነት፤ ቡሩኬና ውዳሴ መመስገን፤ ለእርሱ ይገባዋል። ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን!**

- ❖ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን። ራእ. ፯፥፲፪

____________________________///____________________________